# ዓባይ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር
# Abay Construction PLC

## *የኤችዲፒኢ ፓይፕ እና ጋቢዮን ቦክስ ሰብመርሰብል ፓምፕ ጀኔሬተር እና ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ግዥ የጨረታ ሰነድ*

## *ብሄራዊ ግልጽ ጨረታ (NCB)*

### *የካቲት/2017 ዓ/ም*

# ብሄራዊ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

የጨረታ ቁጥር አኮኃ/የተ/የግ/ማ/ብግጨ/06/17

**አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ኤች.ዲ.ፒ.ኢ ፓይፕ ፣ ሰብመርሰብል ፓምፕ ፣ ሰርፌስ ፓምፕ ፣ ጀኔሬተር ፣ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር እና የጋቢዮን ቦክስ ግዥ በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡**

ስለሆነም ድርጅቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾችን ይጋብዛል፡፡

1. በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የቫት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የሚገዙ ዕቃዎች ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይቻላል፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን አማራ ክልል ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 16 ድባንቄ መድሀኒያለም ቤተክርስቲያን ህዳሴ ሰፈር ታክስ ማዞሪያ 190 ሜትር እልፍ ብሎ አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ቢሮ ከግዥ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 የማይመለስ ብር 200 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ማግኘት ይቻላል፡፡
4. ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች 2% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid Bond) በባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ (CPO) ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) በአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም ማስያዝ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፀው መሰረት የጨረታውን ሰነድ በታሸገ ፖስታ ትክክለኛ ስምና አድራሻ በመፃፍ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ *ለ10 ተከታታይ ቀናት እስከ 10ኛው ቀን 8፡00 ሰዓት* በስራ ሰዓት ከግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይችላሉ፡፡
6. ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ10ኛው ተከታታይ ቀን ከቀኑ በ8፡00 ሰዓት ይዘጋል ፣በ10ኛው ተከታታይ ቀን ከቀኑ 8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 ይከፈታል፡፡
7. 10ኛው ተከታታይ ቀን የበዓላት ቀን ከሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡
8. አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
9. በጨረታው ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ከግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 ድረስ በአካል በመገኘት ወይም በስልክ ቁጥር **https:/www.abayconstruction.org.et/auction-bid/**058 38304460/ 0991021430 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

ድርጅቱ

**ይዘት** **ገጽ**


የተጫራቾች መመሪያ ........ 1
1. ጠቅላላ ........ 1
2. የጨረታ ሰነድ ስለማሻሻል ........ 1
3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /Bid Bond/ እና የውል ማስከበሪያ ........ 2
4. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ እና የውድድር ሁኔታ ........ 2
5. የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ........ 3
6. ራስን ከጨረታ ስለማግለል ........ 3
7. ጨረታ መክፈት፣ መገምገምና አሸናፊ መለየት ........ 4
8. ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ ........ 4
9. የመጫረቻ ሰነድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ........ 5
10. የጨረታ ውጤትን ስለመግለጽና የውል ስምምነት ስለመግባት ........ 5
11. የማቅረቢያ ቦታ ........ 5
12. የውል ማስከበሪያ ........ 6
13. የአቅርቦት መጠን ........ 6
14. አቤቱታ ስለማቅረብ ........ 6

# <u>የተጫራቾች መመሪያ</u>

## 1. ጠቅላላ

1.1. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሙሉ አድራሻ አማራ ክልል ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 16 ድባንቄ መድሀኒያለም ቤተክርስቲያን ህዳሴ ሰፈር ታክስ ማዞሪያ 190 ሜትር እልፍ ብሎ ፡፡

1.2. ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የሚገዛቸው ዕቃዎች **ኤች.ዲ.ፒኢ ፓይፕ ፣ ጋቢን ቦክስ ፣ ሰብመርሰብል ፓምፕ ፣ ጀኔሬተር እና ላፕቶፕ ኮምፒዩተር** ናቸው፡፡

1.3. ተጫራቾች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡

1.4. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከሚዘጋበት ቀን ድረስ ዘወትር በሥራ ሰዓት መውሰድ ይችላሉ፡፡

1.5. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ ማንኛውንም ዓይነት ግብር የሸፈነ መሆን አለበት፡፡

1.6. ድርጅቱ (ግዥ ፈጻሚው) ከክፍያው ላይ የሚቀንሰው 2% ዊዝሆልድ ታክስ ብቻ ነው፡፡

1.7. ተጫራቾች በወጣው የጨረታ ሰነድ ላይ ጥያቄ ወይም ማብራሪያ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 058 38304460/0991021430 በመደወል ወይም በጽሁፍ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 7ኛው ቀን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ግዥ ፈጻሚውም እስከ 7ኛው ቀን ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

1.8. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ሠነድ ላይ ሙሉ ስማቸውን የስልክ፣ የፋክስና የመልዕክት ሣጥን ቁጥራቸውን መጻፍ ይኖርባቸዋል፡፡

1.9. ዋጋ የሚሞሉት በአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በተዘጋጀው ቅጽ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ በራሳቸው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ለመጠቀም የሚፈልጉ ተጫራቾች ካሉ መ/ቤቱ በተሰጣቸው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ የተመለከቱትን በጥንቃቄ ወደ ራሳቸው ቅጽ ማስፈር አለባቸው፡፡ በዚህ ወቅት የመረጃ መዘለል ቢፈጠር የተጫራቹ ሰነድ ከውድድር ውጭ የሚደረግ መሆኑ በቅድሚያ ሊታወቅ ይገባል፡፡

1.10. አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## 2. የጨረታ ሰነድ ስለማሻሻል

2.1. አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ እስከ 7ኛው ቀን ድረስ በሥራ ሰዓት በራሱ ወይም የጨረታ ሰነዱን በገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻነት የጨረታ ሰነዱን ማሻሻል ይችላል፡፡ ከ7ኛው ቀን በኋላ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም፡፡

2.2. የተደረገው ማሻሻያ የጨረታ ሰነዱ አካል የሚሆን ሲሆን በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ሰነዱን ለገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች እና በቀጣይ ሰነዱን ለሚገዙ ሁሉ በተገቢው ሁኔታ በእኩል ጊዜ እንዲደርስ ይደርጋል፡፡

2.3. በጨረታ ሰነዱ ማሻሻያ መሠረትም አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የጨረታ መክፈቻ ጊዜውን እንደ አስፈላጊነቱ እስከ 5 ተከታታይ ቀናት ሊያራዝም ይችላል፡፡

2.4. ተጫራቾች ቀደም ሲል ባስገቡት የጨረታ ዋጋ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በልዩ ሁኔታ መቀነስ ቢፈልጉ ቅድመ ሁኔታ ባልተቀመጠበት አግባብ ካቀረቡት ዋጋ የሚቀንሱትን መጠን በመቶኛ (%) የጨረታው ሳጥን እስከሚዘጋበት ሰዓት ብቻ ፊርማና ማህተም ተደርጎበት ማስገባት ይችላሉ፡፡ ሆኖም የዋጋ ቅናሹ የግልጽ ጨረታ ሥርዓትን የማይጋፋ መሆን አለበት፡፡

## 3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /Bid Bond/ እና የውል ማስከበሪያ

3.1. ተጫራቾች ለሚወዳደሩበት የብር መጠን 2% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /bid bond/ በCPO ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረት የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ***ከዋጋ ማቅረቢያ (ከፋይናንሽያል ሰነድ)*** ጋር በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3.2. ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለ60 ቀናት ጸንቶ መቆየት ይኖርበታል፡፡

3.3. ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ተከፍቶ አሸናፊው ተለይቶና ውል ከተያዘ ጀምሮ ባሉት በ6 ወራት ውስጥ መውሰድ አለባቸው፡፡

3.4. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ይወረሳል፡፡

ሀ. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድር ካገለለ፤

ለ. አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኂላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ፤

ሐ. አሸናፊው እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ 10% ካላቀረበ፤

መ. ተጫራቹ ጨረታውን ለማዛባት የሞከረ መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ፤

3.5. ከላይ በተ.ቁ 3.4 /ሀ-ሠ/ ከተመለከቱት አንዱን የፈፀመ ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ሙሉ ለሙሉ የሚወረስበት ሲሆን በህግም ሊጠየቅ ይችላል፡፡

3.6. የውል ማስከበሪያ(performance bond) ላሸነፉበት ዕቃ 10% በCPO ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 4. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ እና የውድድር ሁኔታ

4.1. ተጫራቾች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ፎቶ ኮፒ እና የሚያቀርቡትን የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተውን የዕቃ ዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ በመጠቀም በተገለፀው ዝርዝር መግለጫ (Detail specification) መሠረት ሰነዳቸውን ስርዝ ድልዝ በሌለበት ሁኔታ ተለይቶ በጥንቃቄና በዝርዝር በመሙላት በመፈረምና በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተም በማድረግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስርዝ ድልዝ ካለም ስለመስተካከሉ ፊርማቸዉን በማስቀመጥ /ፓራፍ/ በማድረግ መረጋገጥ አለበት፡፡

4.2. የጨረታ አቀራረብን በተመለከተ፡-

- ሎት01 በአንድ ፖስታ ቴክኒካልና ፋይናንሻል ኦሪጅናል፣
- ሎት02 በአንድ ፖስታ ቴክኒካልና ፋይናንሻል ኦሪጅናል፣
- ሎት03 በሁለት ፖስታ ቴክኒካል ኦሪጅናል እና ፋይናንሻል ኢሪጅናል፣
- ሎት04 በሁለት ፖስታ ቴክኒካል ኦሪጅናል እና ፋይናንሻል ኢሪጅናል፣

4.3. ውድድርን በተመለከተ **በየሎቱ በእያንዳንዱ የእቃ አይነት በነጠላ ዋጋ** አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

4.4. በማሸጊያ ፖስታ ላይ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስፈር ያስፈልጋል፡፡

ሀ. የጨረታው ዓይነትና ቁጥር፣.............................

ለ. ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት ስምና አድራሻ፣....................................

ሐ. የተጫራቹ ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ ፊርማና ሙሉ አድራሻ፣..........................

4.5. በፖስታ የሚላክ የመጫረቻ ሰነድ በመዘግየቱና በጥንቃቄ ካለመታሸጉ ጋር በተያያዙ ችግሮች ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡

## 5. የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ

5.1 ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተገለፀው የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በፊት የመጫረቻ ሰነዱን በተዘጋጀው የጨረታ ቦታ እና የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸው ብዛት ያላቸው ከሆኑና በጨረታ ሳጥኑ ውስጥ ማስገባት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ በድርጅቱ የግዥ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 በመገኘት ለተመደበው ግዥ ኦፊሰር ማስረከብ ይችላሉ፡፡ ተረካቢውም የተጫራቹን ስምና አድራሻ እንዲሁም የተረከበበትን ቀንና ሰዓት በመመዝገብ ለመረከቡ ማረጋገጫ (ማስረጃ) የሚሰጥ ሲሆን በግዥ ኦፊሰር የተሰበሰቡ የመጫረቻ ሰነድ ፖስታዎችን ጨረታው ከመዘጋቱ 30 ደቂቃ በፊት ለግዥና ጨረታ ኮሚቴው ርክክብ ያደረጋል፡፡

5.2 በጨረታ ሰነዱ መሰረት የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት ደርሶ የጨረታ ሳጥን ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተጫራቹ በአካል ከቀረበ በተጫራቹ እጅ እንዳለ በሌላ አግባብ የመጣ ከሆነም ሳይከፈት ለተጫራቹ /ለአቅራቢው/ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## 6. ራስን ከጨረታ ስለማግለል

6.1 ተጫራቾች የጨረታ ሳጥኑ ከመዘጋቱ ቀንና ሰዓት በፊት ራሳቸውን ከጨረታው ማግለል ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ራሳቸውን ከጨረታው ስለማግለላቸው በሚያቀርቡት ሰነድ ላይ የድርጅቱ ህጋዊ ማህተም ማድረግና ሙሉ ስማቸውን መጻፍ ይኖርባቸዋል፡፡ የጨረታ ሰነዱን የሚሞሉና የሚፈርሙ ተወካዮች ከሆኑ ሕጋዊ የውክልና ማስረጃቸውን የተገናዘበ

ፎቶ ኮፒ ከሚቀርበው ሰነድ ጋር በማያያዝ በፖስታ አሽገው የጨረታ ሳጥኑ ከመዘጋቱ በፊት በጨረታ ሳጥኑ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

6.2 የጨረታ መዝጊያ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡

## 7. ጨረታ መክፈት፣ መገምገምና አሸናፊ መለየት

7.1. የጨረታው አየር ላይ ቆይታ 10 ተከታታይ ቀናት ሲሆን ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ10ኛው ቀን ከቀኑ 8:30 ሰዓት በመ/ቤቱ የግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት በግልፅ ይከፈታል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ጨረታው በሚከፈትበት ቦታ፣ ቀንና ሠዓት በራሳቸው ምክንያት ባይገኙ ጨረታው እንዲከፈት በማድረግ ውድድሩ ይካሄዳል፡፡

7.2. ጨረታዉ ሲከፈት በንባብ የሚሰሙ የተጫራቾች ሥም፣ የተወዳደረበት ምድብ (ሎት)፣ የሚደረግ የዋጋ ቅናሽ ካለ መጠኑንና ሁኔታውን በሚመለከት (ቅድመ ሁኔታ ያልተቀመጠበት እና የጨረታ ሥርዓቱን የማይጋፋ መሆኑን)፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ዓይነትና መጠን እንዲሁም ሌሎች እጩ ተወዳዳሪዎች ደረጃቸውን ለማሳወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰቡ መሰረታዊ ነጥቦች በጨረታው መክፈቻ ወቅት ለተጫራቾች ይነበባሉ፡፡

7.3. በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የቀረቡትን የጨረታ ሰነዶች በመገምገም ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከተጫራቾች ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚጠየቀውና የሚሰጠው ማብራሪያ በሁሉም ተጫራቾች እንዲታወቅ በፅሁፍ ሆኖ ተጫራቾች ካቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ ዋጋውን ወይም የሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለወጡ ማለትም በሌሎች ተፎካካሪ አቅራቢዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ መሆን የለባቸውም፡፡

7.4. በግምገማ ወቅት በነጠላ ዋጋና በጠቅላላ ዋጋ መካከል የዋጋ ልዩነት ቢኖር በነጠላው ዋጋ መሠረት በማስተካከል ይገመገማል፡፡

7.5. በግምገማ ወቅት ዋጋው በአኃዝና በፊደል በሚገለጽበት ወቅት ልዩነት ቢኖር በፊደል በተገለጸው መሠረት በማስተካከል ይገመገማል፡፡

7.6. ከተጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርትና ከዚያ በላይ ቴክኒካል መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾች መካከል ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው አሸናፊ ይመረጣል፡፡

7.7. ወድድሩ ቴክኒካል መስፈርት አሟልቶ በእያንዳንዱ እቃ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

## 8. ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ

8.1 በጨረታ የተወዳደረው አቅራቢ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፈለገውን አነስተኛ የጥራት መመዘኛ መስፈርት ያላሟላ በመሆኑና ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፤

8.2 ተጫራቹ በአንዱ ዋጋና በጠቅላላ ዋጋው መካከል የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል ሲሆን፤

8.3 ተጫራቹ ያቀረበው የመጫረቻ ሰነድ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ፤

8.4 በተራ ቁጥር 1.2 የተዘረዘሩትን የጽሁፍ ማስረጃዎች እንዲሁም በተጨማሪ ሌላ ተፈላጊ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተጠይቆ ከጨረታ ማቅረቢያ ሰነዱ ጋር ወይም በበቂ ምክንያት በጨረታ ግምገማ ወቅት ማቅረብ ካልቻለ፤

8.5 ተጫራቾች የግዥ አካሄዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፤

8.6 የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተጠይቆ ያላስያዘ እንደሆነ፤

8.7 ተጫራቾች ዋጋ አቀራረብ/አሞላል እና የምድብ/የሎት ምርጫን በሚመለከት በተጠየቀው መሰረት ሞልተው ካላቀረቡ፡፡

8.8 የአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የግዥ መመሪያ እና ይህን የጨረታ ሰነድ የሚጥሱ ድርጊቶች መፈፀሙ የተረጋገጠ ከሆነ፤

## 9. የመጫረቻ ሰነድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ

9.1 የመጫረቻ ሰነድ እስከ 60 ቀናት ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡

9.2 ግዥ ፈጻሚ መስሪያ ቤት የመጫረቻ ሰነዱ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲራዘምለት ከፈለገ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በጽሁፍ በመጠየቅ ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡ ሆኖም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ካልተስማሙ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ዉድድር እንዲሰረዙ ይደረጋል፡፡

9.3 የቀረበላቸውን የመጫረቻ ሰነድ የመቆያ ጊዜ ማሻሻያ ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች መቀበላቸውንና ጊዜውን በመጥቀስ በጽሁፍ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚህ ጨረታ ያስያዙት ዋስትና መቆያ ጊዜ አብሮ እንዲሻሻል ማድረግ ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡ የጨረታ ዋስትናውን ያላሻሻለ ተጫራች የጨረታ ሰነዱን ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውጭ ይደረጋል፡፡

## 10. የጨረታ ውጤትን ስለመግለጽና የውል ስምምነት ስለመግባት

10.1 ማንኛውም የጨረታ ግምገማ ውጤት በሚመለከታቸው አካላት በጸደቀ በዕለቱ ለተመረጡ በአድራሻቸው በደብዳቤ እና በውስጥ የማስታወቂያ ሰሌዳ የሚገለጽ ሲሆን ላልተመረጡ ተጫራቾች ደግሞ በውስጥ የማስታወቂያ ሰሌዳ ያልተመረጡበትን ምክንያት በማካተት በእኩል ጊዜ ለሁሉም ይገለጻል፡፡

10.2 አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ እና የግዥ ውል እንዲፈጽም ከአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ደብዳቤ በደረሰው ከ3 የስራ ቀናት የቅሬታ ጊዜ በኋላ ባሉት 5 የስራ ቀናት ውስጥ 10% የውል ማስከበሪያ በሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በማስያዝ የዕቃ አቅርቦት ውል ከግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ጋር መፈራረም አለበት፡፡

10.3 በጨረታ አሸናፊ የሆነው ተጫራች የአቅርቦት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ በመውረስ ከሌሎች ፈቃደኛ ከሆኑ ተጫራቾች ጋር በየደረጃቸው ቅደም ተከተል በአንደኛው ዋጋ ውል በመያዝ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡፡

10.4 በጨረታው አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው አቅራቢ ድርጅት **በሎት 1 ከተዘረዘሩት እቃዎች ውስጥ ኤችዲፒኢ ፓይፕ** አቅርቦትን በተመለከተ ከተስማሚነት ምዘና ኤጀንሲ የጥራት ማረጋገጫ ዋስትና ማቅረብ አለበት በተጨማሪም የሳምፕል የጥራት ምርመራ ተረጋግጦ ርክክብ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 11. የማቅረቢያ ቦታ

11.1 የማቅረቢያ ቦታ በውል ጊዜው የተዘረዘሩትን እቃዎች **በሎት** 1 የተጠቀሰው **ኤችዲፒኢ ፓይፕ** በእያንዳንዱ የፕሮጀክት መገኛ አድራሻ መሰረት ሲሆን ሌሎች **በሎት** 2 ፣ **በሎት** 3 ፣ **በሎት** 4 የተጠቀሱት እቃዎች ባህር ዳር ከተማ ከሚገኘው ከግዥ ፈጻሚው መ/ቤት (አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር) መጋዘን ይሆናል፡፡

## 12. የውል ማስከበሪያ

12.1 አሸናፊ ተጫራቾች ማቅረብ ያለባቸው የውል ማስከበሪያ መጠን ያቀረቡትን ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ (ፐርፎርማንስ ቦንድ) በባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ /CPO/ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (unconditional bank guarantee) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

## 13. የአቅርቦት መጠን

13.1 በጨረታ ሰነዱ ላይ የተጠየቀውን የዕቃ መጠን በውል ወቅት እስከ 20% በመጨመር ወይም በመቀነስ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከውል በኋላ እስከ 30% ተጨማሪ የግዥ ትዕዛዝ በመስጠት ግዥ መፈጸም ይቻላል፡፡

## 14. አቤቱታ ስለማቅረብ

14.1 በጨረታ ሂደቱ ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል የሚል ወይም በጨረታው ግምገማ ውጤት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት የጨረታ ውጤት ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሥራ አስኪያጅ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

14.2 አቤቱታ የቀረበበት መ/ቤትም ምላሹን በቀረበለት በ3 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው መልስ ይሰጣል፡፡

14.3 በአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስራ አስኪያጅ ውሳኔ ያልረካ አቅራቢ በፍርድ ቤት ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡

14.4 በተራ ቁጥር 14.1 ከተሰጠው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

Abay Construction PLC ቁ.5

**Lot -01 HDPE PIPE Price form**

| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የማስረከቢያ ቦታ | የአንዱ ዋጋ ከትራንስፖርት ጋር እና ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከትራንስፖርት ጋር እና ቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | HDPE PE100 Pipe | .OD400mm PN10 | Meter | 1210 | ሰ/ወሎ ከወልድያ ሙጃ ታላቅ ወንዝ መስኖ ፕሮጀክት 75 ኪ/ሜ | | | |
| 2 | HDPE PE100 Pipe | .OD355mm PN10 | Meter | 760 | | | | |
| 3 | HDPE PE100 Pipe | .OD200mm PN10 | Meter | 150 | | | | |
| 4 | HDPE PE100 Pipe | .OD180mm PN10 | Meter | 520 | | | | |
| 5 | HDPE PE100 Pipe | .OD160mm PN10 | Meter | 400 | | | | |
| 6 | HDPE PE100 Pipe | .OD140mm PN10 | Meter | 1320 | | | | |
| 7 | HDPE PE100 Pipe | .OD125mm PN10 | Meter | 330 | | | | |
| 8 | HDPE PE100 Pipe | .OD110mm PN10 | Meter | 690 | | | | |
| 9 | HDPE PE100 Pipe | .OD90mm PN10 | Meter | 400 | | | | |
| 10 | HDPE PE100 Pipe | .OD75mm PN10 | Meter | 500 | | | | |
| 11 | HDPE PE100 Pipe | .OD63mm PN10 | Meter | 315 | | | | |
| 12 | HDPE PE100 Pipe | .OD400mm PN10 | Meter | 140 | ከደ/ብርሃን ደብረ ሲና አይራራ መስኖ ፕሮጀክት 55 ኪ/ሜ | | | |

| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የማስረከቢያ በታ | የአንዱ ዋጋ ከትራንስፖርት ጋር እና ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከትራንስፖርት ጋር እና ቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | HDPE PE100 Pipe | .OD110mm PN16 | Meter | 1260 | ከባህር ዳር ቋራ ወረዳ ፈርሻዎ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት 225 ኪ/ሜ | | | |
| 14 | HDPE PE100 Pipe | .OD110mm PN10 | Meter | 1440 | | | | |
| 15 | HDPE PE100 Pipe | .OD90mm PN10 | Meter | 150 | | | | |
| 16 | HDPE PE100 Pipe | .OD75mm PN10 | Meter | 4800 | | | | |
| 17 | HDPE PE100 Pipe | .OD63mm PN10 | Meter | 9600 | | | | |
| 18 | HDPE PE100 Pipe | .OD50mm PN10 | Meter | 1400 | | | | |
| 19 | HDPE PE100 Pipe | .OD40mm PN10 | Meter | 5800 | | | | |
| | Total price | | | | | | | |

- የተወዳዳሪው ድርጅት ሙሉ ስም.................................................................................
- አድራሻ ...................................................................................................
- ስልክ ቁጥር ......................................................................................................
- የማስረከቢያ በታ በተጠቀሱት **ፕሮጀክቶች መጋዘን ድረስ**
- ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት
- ድርጅቱ ተቀናሽ የሚያደርገው 2% (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብቻ ነው።

## Lot -02 GABYON BOX Price form

| No | የዕቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለ ኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | gabion Box 2m*1m*1m **Fabricated** | 16kg/pcs,8cm*10cm hole diameter, mish wire with 2.5mm dia,zinc coated galvanized wire,Boulder Ø3mm and triple Twisted hexagonal woven wire mesh | pcs | 1590 | | | Gista,Samba, Gelda projects |
| 2 | gabion Box 1m*2m*2m **Fabricated** | 18kg/pcs,8cm*10cm hole diameter, mish wire with 2.5mm dia,zinc coated galvanized wire,Boulder Ø3mm and triple Twisted hexagonal woven wire mesh | pcs | 20 | | | samba |
| 3 | gabion Box 1m*1m*1m **Fabricated** | 9kg/pcs,8cm*10cm hole diameter, mish wire with 2.5mm dia,zinc coated galvanized wire,Boulder Ø3mm and triple Twisted hexagonal woven wire mesh | pcs | 747 | | | Enezer,samba,Gelda |
| 4 | gabion Box 0.5m*1m*2m **Fabricated** | 12kg/pcs,8cm*10cm hole diameter, mish wire with 2.5mm dia,zinc coated galvanized wire,Boulder Ø3mm and triple Twisted hexagonal woven wire mesh | pcs | 404 | | | Talak wonz |
| 5 | gabion Box 1.5m*1m*1m **Fabricated** | 13kg/pcs,8cm*10cm hole diameter, mish wire with 2.5mm dia,zinc coated galvanized wire,Boulder Ø3mm and triple Twisted hexagonal woven wire mesh | pcs | 700 | | | gelda |
| 6 | Gabyon Tying wire | 2.5mm thickness galvanized wire | kg | 1322 | | | Enezer,samba,Gelda |
| | | Total price | | | | | |

የተወዳዳሪው ድርጅት ሙሉ ስም.........................

ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት .

ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት

የማስረከቢያ ቦታ ባህር ዳር አባይ ኮንስትራክሽን መጋዘን ድረስ

| | Lot -03 Pump and Generator | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| No | የዕቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የተመረተበት አገር (Country of Origin) | የምርቱ መጠሪያ ስም (Brand Name) | ሞዴል (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
| 1 | Submersiable pump 9.2kw | electric slurry Submersiable raw water /Dewatering pump with appropriate cololing sleeve and motor of 380v-400 v, 50Hz impedance type or equvalent starting type complete with non return valve ,3" Threaded pump out let is <or> 3" the reduce must be medium duty GS) including level sensorcontrol electrode 93) for each board and appropriate factory assembled control panel board with Q=9.8L/s, H=52m, pump power9.2kw, 2900rpm, pump efficency at duty point should be 65% .Maximum pumpwith motor length including cooling sleeve should be 3.5m | set | 2 | | | | | | shala wsp |

| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የተመረተበት አገር (Country of Origin) | የምርቱ መጠሪያ ስም (Brand Name) | ሞዴል (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | Submersiable pump 11kw | electric Submersiable pump with motor of 380v/400 v, 50Hz impedance type starting with non return valve ,3" Threaded if the pump out let > or < 2 1/2" the reduce must be Heavy duty GS) it including 3 pcs level control electrode and appropriate control panel Board.<br>with Q=41/s, H=187m, pump motor power < 11kw, pump efficency at duty point should be > 70% . as specfird detail in the Trchnical spesfixation | set | 1 | | | | | | Fershaho wsp |

| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የተመረተበት አገር (Country of Origin) | የምርቱ መጠሪያ ስም (Brand Name) | ሞዴል (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | Surface pump 26kw | Multi stage centrifugal side or end suction & radial or side discharge surface pump (1+1), with Q=9.81/s, THD=149m, pump power 26kw, pump efficency at duty point 65% , 3phase, squirre cage,induction type, 380/400v, 50hz concentricreducer DN80 PN10 to fitt pump delivery side and ecentric reducer DN100PN10 to fit pump suction side including pump manufacturer starting control panel board, and all other accessories necessary for the complete Instaliation and operiation manual of the pump .NPSHR < 6.6m(@booster) | set | 2 | | | | | | shala wsp |

Abay Construction PLC

| *No* | *የእቃው አይነት* | *ዝርዝር መግለጫ* | *መለኪያ* | *ብዛት* | **የተመረተበት አገር** (Country of Origin) | **የምርቱ መጠሪያ ስም** (Brand Name) | **ሞዴል** (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | Generator 85KVA | Diesel generator set, continuous rating , as per the technical spesfication, engine and alternator pre - installed on the common regid frame, switch gear panel, day tank incorporated in to the frame ,exhaust piping system including manufacturer working, service & maintenance manual , spare part catalogue filter, 2pcs air cleaner , 2 pcs fuel filter and 2pcs oil filter,belt ,electrical and mechanical tool kit 80 pcs,and all accessories required forinstaliation with prime power =85KVA, 3phase , 400v,50hz | set | 1 | | | | | | shala wsp |

ቁ.5 Abay Construction PLC

| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የተመረተበት አገር (Country of Origin) | የምርቱ መጠሪያ ስም (Brand Name) | ሞዴል (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | Generator 30KVA | Open type Diesel generator set, continuous rating , as per the technical spesfication, engine and alternator pre - installed on the common rigid frame, switch gear panel, day tank incorporated in to the frame ,exhaust piping system including manufacturer working,service&maintenance manual , spare part catalogue and all Accessories required for installation with prime power =30KVA ,Three phase ,400v ,50hz,1500RPM as specified detail in the Technical specification 2 pcs fuel filter , 1pc oil filter, 1pc air cleaner , and, 1electrical and mechanical tool kit | set | 1 | | | | | | Fershaho wsp |
| | | | | | | Total Price | | | | |

የተወዳዳሪው ድርጅት ሙሉ ስም

አድራሻ ......

የማስረከቢያ ቦታ አባይ ኮንስትራክሽን መጋዘን ድረስ

ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት

ድርጅቱ ተቀናሽ የሚያደርገው 2% (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብቻ ነው፡

አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር Bid No AC/OB/06/17

Abay Construction P/ Lted Company Bahir Dar Ethiopia

| | Lot -04 Laptop Computer | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ***No*** | *የእቃው አይነት* | *ዝርዝር መግለጫ* | *መለኪያ* | *ብዛት* | **የተመረተበት አገር** (Country of Origin) | **የምርቱ መጠሪያ ስም** (Brand Name) | **ሞዴል** (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
| 1 | Laptop Computer | HP Lapptop pavilion copmuter Core i7,Processor speed 1.7GHZ,&above 12th generation , RAM,16GB, SSD-1TB capacity, 2GB Graphics card based on attachments. | pcs | 4 | | | | | | |

- የተወዳዳሪው ድርጅት ሙሉ ስም
- አድራሻ ......
- የማስረከቢያ ቦታ አባይ ኮንስትራክሽን መጋዘን ድረስ
- ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት
- ድርጅቱ ተቀናሽ የሚያደርገው 2% (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብቻ ነው፡